<u>ተነሱ እንነሳ(አዳነ መኮነን)</u>



እንደ ትናእት ናው ዛሬም እንነሳ
ዝም ብለን አንይ ሲከፍሉን በጎሳ።
ኢትዮጵያ ወድቃለች እረዳት በማጣት
ተነሱ እንነሳ ደግፈን እናንሳት
አንድ ሁለት ሳንል ሁላችን በህብረት
ከገባችው አዘቅት ጎትተን እናውጣት
ከወደቀችበት ታግለን ነጻ እናውጣት።
በውጭም ያለነው ያላችሁ ባገር ቤት
ዳግም እንዳትወድቅ እናመቻችላት
ከዓለት ላይ ቆፍረን ቤቷን እንሥራላት
ኢትዮጵያ ሀገራችን የሁሉም እናት ናት።
ለአንድ ለሁለት አይደለም ለሁሉም ነው ጉዳት
ተነሱ እንነሳ በአንድ ላይ በህብረት
መለያየት ይቅር ፍቅር እንመሥርት
ለሁላችን ነው ጥቅምም ሆነ ጉዳት
የሚደርስብን ሁልጊዜ ዕለት በዕለት።
ገብተው ሲዘርፉነ ቁጭ ብለን በማየት
በሩን እየከፈትን ሌባ አስገባነበት
ከማንም አይደለ ከእኛ ነው ያለ ጥፋት።
የሌላ ይመስል ሲዘረፍ ንብረት
ተዘግቶ የኖረን በር በመከፈት
ተባባሪ ሆኖ መንገድ በመምራት
አሳልፎ ሰጠ የአባቱን ርስት።
ሌላው ተቀምጦ አንዱ እየሞተላት
ለማን ነው የምተሆን ይች ሀገር ወደፊት
ጩሆት እያሰማች በአራቱ መዓዝናት
ቁጭ ብሎ ማየቱ አይጠቅምም ለእናት
ሁላችን እንነሳ አሁን እንድረስላት
ባዕዳ ይመስል ቁጭ ብለን አንያት።

በሌሎች ያየነው እንዳይደረስ በእኛ
ካሁኑ እንዘጋጅ እንንቃ አንተኛ።
በአንድ ላይ በህብረት መሆኑ ይሻላል
ከመጥቀሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኗል
መከፋፈል ይቅር ሲጎዳን አይተናል።
ስም እያወጣችሁ ብትለጣጠፉባት
የስም መብዛት ለእርሷ ሰላምም አይሰጣት
ከጥንት ጀምሮ እርሷ ግን አንዲት ናት
የሦስት ሺህ ዘመን ትልቅ ታሪክ ያላት
የጀግኖች ሀገር እምዬ ኢትዮጵያ ናት።
ከዛ ጀምሮ ነው አለሙ የሚያውቃት
እናት ኢትዮጵያ የሁሉም አገር ናት።
ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሳንከፋፈል
ኦሮሞ፤ አማራ ፤ትግሬ ሳንባባል
እንደ ጥንት አባቶች እንሰለፍ እኩል
ሁላችን እንነሳ ለኢትዮጵያ ስንል
ሰው የዘራውን ዘር እራሱ ያጭዳል።
ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው
እንደ ሚሉት አበው
ወያኔ በለኮሰው እሳት ይቃጠላል ከዚያው።

ዛሬ አንድነት የጠራውን የሪታ ቀን፤ ሁሉም የፖለቲካ ተቃዋሚዎች እንዲደግፉና አብረው እንዲሰለፉ፤ የኦሮሞ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ፤በጎንደር አካባቢ የሚታየው እንቅስቃሴ፤ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በተናጠል የሚያደርጉት ትግል ብቻውን የሚያመጣው ውጤት እንደሌ ተገንዝበው ትግሉን አቀናጅተው ኢትዮጵያን ከጥፋት እንዲያድኗት። እንዲሁም የኢትዮጵያ መስሊሞች የሃይማኖትን ጥያቄ ወደ ሀገር ቀይረው ትግላቸውን እንዲገፉበት፤ ምክንያቱም በሀገር ነጻነትና ሰላም ከሌለ በሃይማኖትም ነጻነት እንደማይገኝ ተረድተውና ዛሬ የአንዱ በትር ነገም ለሌላው እንደሚደርስ አውቀው ትግላቸውን በህብረት እንዲያደርጉት ስል በዚህው ጥሪየን አስተላልፋለሁ።

ሀገራችን ከጥፋት፤ህዝባችንን ከእልቂት፤ እግዚአብሔር ይጠብቅልን!!!

ሚያዝያ፤፳፮፡ቀን፤፪ሺ፮፤ ዓ/ም (04/05/2014)